# አዛለች ወደ ፓርላማ (የምርጫ ጭውውት)

## ክፍል ሦስት









ባላፈው መጋቢት- የአቦለት ቤተክሲያን
ጠጋ ብዬ ጠየቅሁ- ወረቀት ሲበተን
እንዲህ ይነበባል- በራሪው ወረቀት
ከላይ ምርጫ ብሎ- ከታች ንብ አለበት፤

አዛል ምርጫ ገባች- ሹርባ ተሰርታ
መረራ ጉዲናን- በድምፅ ልትረታ
ኢህአዴግ ፓርቲዋን- ወክላ ቀርባለች
ልማታዊቷ ሴት ምረጡኝ- ትላለች።

ፎቶውን አይቸ -
አንገቴን አቅንቸ
መፈለግ ጀመርኩኝ- አዛሉን ጓጉቸ።
መስቀል ሲሳለሙ- አየኋችውና- ለብሰው ጃኖ ኩታ
መንገዴን ቀጠልኩኝ- ከቆሙበት ቦታ።

“ዶ/ር አዛሉ! ዶ/ር…”- ብዬ ስጠራችው
የፌደራል- ፖሊስ ወገቤን ዠለጠው
“አተ… አታ ባለጌ” - ብሎ ሲጮህብኝ
መሬት ተሰንጥቃ- ትውጥ ተመኘሁኝ።

እኝህማ አዛሉ- እኔ የማውቃቸው
ጠላ ኮማሪዋ -አይደሉ እንዴ እሳቸው።

ፖሊስ ቢዠልጠኝ- በያዘውም ዱላ
ምን ሊባል -ይገባል ከብልግና ሌላ
እንዲህ ያለ- ጥሪ “ዶክተር!” ብሎ ማለት
ስድብ ብቻ ሳይሆን- ብልግናም አለበት
ከአንድም ሁለት ጊዜ- ለቀበሌ ሸንጎ
ራቦል ጥፌያልሁ- ለአዛለች ሸመኮ

ማንበብና መፃፍ- የማያውቁትን ሴት
ዱላ እማይበቃው ነው-ዶክተር ብሎ መጥራት
ፖሊስ አዋከበኝ- ዶለኝ ወኽኒ ቤት
አዋርደል ተብዬ- ልማታዊቷን ሴት።

******

ሁለት ወር ታስሬ - የተፈታሁኝ ቀን
አሸነፋን ሰማሁ- አዛሉ መረራን።

የሰፈራችን ሹም- የወያኔው ኔጭ ሹም
እንዲህ አርጎ አሰማኝ- መቸም ጉድ አያልቅም።

“የሰፈር ወይዘሮ- የጠላ ኮማሪ
የትናንት ልማት ሴት- ስራን አስተማሪ

ማንበብ መጻፍ ባይኖር- ማይምም ቢሏቸው
ሃገር መገንባትን- ዲሞክራሲ አውቀው
የመንግስት አመራር- በደንብ ገብቷቸው
አዛሉ ዶክተሩን- ጥለው አሳይዋቸው
ፖለቲካ ሳይንስ- ዓለም አቀፍ ቢሉ
ዶክተር መረራ ነኝ- የታወቅሁት ቢሉ
መረራ ተረታ- ድል ሆነ በአዛሉ።

ወይዘሮ አዛለች ነች- የሆነች አንበሳ
እንግዲህ በጀ በል- አምቦም እጅ ንሳ።

አሜሪካን ሃገር ያለሽው ሂላሪ
ይልቅስ ነይና- ከአዛለች ተማሪ።"

በስጨትጨት ብየ- እልሄ መጣና
መናገር ጀመርኩኝ- ተራዬ ሆነና።

"ገና ዱሮ ነበር- ያኔ ሳይወጠን
አልነጋም ያልናቸው- የዛሬውን አይተን።

መለስ ወንፊት ሰፍቶ- ማበጠር አቅዶ
ልደቱ እህል ሆኖ- ሃይሉም ገብቶ ወዶ
ይኸው ተበጠረ- መረራም ወረደ
ግፍም ህግ ሆነና- ውሸት ተለመደ።"

ብዬ ተናግሬ- ልጨምር ስሞክር
ሰውር ፖሊስ ኖሮ- ከነጭ ለባሹ ጋር
ሸጉጡን አውጥቶ- እያንገራገረ- ማጅራቴን ይዞ
እስር ቤት ጨመረኝ- በመኪና አግዞ።

ዳግማዊ ዳዊት
ግንቦት 2002
Ethio_dagmawi@yahoo.com